በክልሉ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ በአደረጃጀት ተዋቅሮ ወደ ስራ ሲገባ የራሱ የሆነ የአፈጻጸም ችግር የነበሩበት ሲሆን በተለይ ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ በነበረዉ አደረጃጀት በሰዉ ሀይል ሽፍኖ ስራዎችን ለማከናወን በሚደረግ ጥረት ውስጥ ባለሙያውየተሻለ ደመወዝ ፍለጋ ከፍተኛ ሥራ መልቀቅ በመኖሩ በስራ ላይ የራሱ የሆነ ተጽዕኖ ፈጥሮ ቆይቷል። ይህንን ችግር ለመፍታት ከ2009 ዓ.ም በኋላ ባለሙያዎችን የሚስብ አደረጃጃትና ጥቅማ-ጥቅም ከግምት በማስገባት የክልሉ መንግስት ለሴክተሩ በሰጠዉ ትኩረት ወደ ኤጀንሲ በማደጉ ችግሮችን ለመቅረፍ አስተዋፆ እያደረገ ይገኛል።

በክልሉ በተለያዩ ተቋማት የሚገኙ ሰራተኞችን መሰረታዊ የኮምፒዉተር እዉቀት በመስጠት ከመረጃ ቴክኖሎጂ ጋር ትዉዉቅ ለመፍጠርና የመረጃ አያያዙን ቀልጣፋና ጥራት ያለዉ ለማድረግ በክልል ለሚገኙ 3637 ባለሙያዎች አድቫንስና የመሰረታዊ ኮምፒዩተር ክህሎት እንዲሁም የኮምፒውተር ጥገናና በውጤት ተኮር እቅድ ዙሪያ ላይ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል።

የመረጃ ቴክኖሎጂን ከከተማ እስከ ገጠር ለማድረስ በሚደረገዉ ርብርብ የገጠሩን ህብረተሰብ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለማድረግ የገጠር ኢኮቴ ማዕከላትን በማደራጀት፤ የገጠር ሽቦ አልባ ስልኮች ክትትል ማድረግ፤ የወረዳ ኔትና ስኩል ኔት፤ ሁለገብ የማህበረሰቡ መረጃ ማዕከላት ሽፋን ማስፋትና የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነትን ባህል ለማሳደግ ባለፉት የዕቅድ ዘመን በሁሉም ወረዳዎች22የማህበረሰብ መረጃ ማዕከላት የተቋቋመ ሲሆን፣ 21 የገጠርኢኮቴ መረጃ ማዕከላት፤ሁለት የማህበረሰብ ሬድዮ የተቋቋመ በመሆኑ ህብረተሰቡ በአንስተኛ ዋጋ ባለበት ቦታ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ሆኗል። የገጠሩን ማህበረሰብ የአይ.ሲቲ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለማድረግ 138 በገጠር ኢኮቴ ማዕከላት የተደራጁ ወጣቶችንና ማህበረሰብ በአጠቃላይ አቅም ለመገንባት የተቻለ ሲሆን 460 ቀበሌዎች የሽቦ አልባ ስልክ እንዲገባ ተደርጓል።

ቀደም ሲል በ20 ወረዳ የተቋቋመዉ የወረዳ ኔት አገልግሎት በክፍያ ምክንያት በመቋረጡ2,140,618.79 ብር ክፍያ በመፈጸም ባክ አፕ ዳታ /Back up data center/ በተሟላ ሁኔታ ስራ ለማስጀመር ጥረት ቢደረግም ሜን ዳታ ሴንቴር /Main data center /ሙሉ በሙሉ ስራ ባለመጀመሩ የወረዳ ኔት አገልግሎት በ4 ወረዳዎች ብቻ እንዲሰጥ እየተደረገ ይገኛል።የቪድዮ ኮንፈረስ አገልግሎትን በተመለከተ ባለፉት የበጀት አመታት ለ7 መ/ቤቶች አገልግሎት የተሰጠ እና በአገልግሎቱ 283 ሰዎች ተጠቃሚ ሲሆኑ ቢያንስ ለስብሰባው ይወጣ የነበረ 158,520 ብር ወጪ ለማስቀረት ተችሏል።

የእድገትናትራንስፎርሜሽን እቅድ አመት መጨረሻ ድረስ ለ5 መ/ቤቶች ውስብስብ ያልሆነ የኢንተርኔት ኔትዎርክ/ መረጃ መረብ/ የተዘረጋ ሲሆን 8 መ/ቤቶች ደግሞ ውስብስብ ያልሆነ ሶፍትዌር /ዳታ ቤዝ / ልማት ተከናውነዋል። በ37 ት/ቤቶች ስኩል ኔት፣ ለ9 ት/ቤቶች የክላውድ ኮፒቲንግ ተግባራዊ የተደገረ ሲሆን የኢኮቴ መሳሪዎችጥገና በተመለከተ በክልል ደረጃ ካሉት ሁሉም ሴክቴር መ/ቤቶች 361 የኢኮቴ መሳሪዎችን ጥገና እንዲሁም የ24 ፕላዝማ ጥገና የተደረገ ሲሆን በኤጀንሲው ባይጠገን ኑሮ በዚሁ ስራ ምክንያት ይባክን የነበረው የመንግስት ወጪ በጥሬ ገንዘብ ሲተመን

333,260 ብር ወጪ ለመቀነስ የተቻለ ከመሆኑም በላይ ለ6 ሴክቴር መ/ቤቶች የኢኮቴ መሳሪዎች ግዥ ለመፈጸም የስፔስፊከሽን ዝግጅት ለማድረግ ተችለዋል።

ከክልሉ፤ከወረዳና ከከተማ አስተዳደር ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ፤ ጋር በመተባበር ለአዳዲስ እና ነባር የኢ.ኮ.ቴ ንግድ ተቋማት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የአሠራር ስርዓት በመዘርጋት በስታንዳርዱ መሠረት ለ152 በአይ.ሲ.ቲ ንግድ ዘርፍ ለተሰማራ ተቋም ክትትል በማድረግ የብቃት ማረጋገጫ ተሰጥቶል። ቅንጂታዊ አሰራርን ለማጎልበትና ለተሻለ አገልግሎት ተደራሽነት ከ3 ባለድርሻ አካላት (ኢትዮ-ቴሌኮም፤ትምህርት ቢሮና ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ) የጋራ መግባቢያ ስምምነት ሰነድ በማዘጋጀት ለመፈራረም ቢታሰብም ከትምህርት ቢሮ ጋር ብቻ ለመፈራረም ተችሏል።

መንግስት ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ወደ ኤጀንሲ ማሳደጉ፣በዘርፉ ልማት ላይ ትኩረት የሚያድረጉ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መኖራቸውና ባለሙያዎችን ማፍራታቸው፣በዘርፉ ለሚካሄዱ የፈጠራና የምርምር ስራዎችን የሚደግፍና የሚያበረታታ ስርዓት መኖሩ፣የዘርፉ ፖሊሲና እስትራቴጂ መኖሩ እንደ መልካም አጋጣሚ ይታያሉ።

የኤጀንሲዉን ዋና ራዕይና ተልኮ የክልሉን ህበረተሰብ የቴክኖሎጂ ተደራሽና ተጠቃሚ ማድረግ ቢሆንም በBPR ጥናት መሠረት የተፈቀደዉ የሰዉ ሃይል ባለመሟላቱ፣ የባለሙያ አቅም ውስንነት፤የሳይንስና ኢኖቬሽን ዘርፍ BPR ጥናት ያለመጠናቀቁ፤ የተሟላ ፋሲሊቲ አለመኖር፣ቴክኖሎጂ ዘርፍ ከሚያስፈልገዉ በጀት አንፃር የሚመደበዉ በጀት አናሳ መሆን፤ለስልጠና እና ለጥገና የሚያገለግል የተሟላ የማሠልጠኛ ማዕከል አለመኖር፤በዞንና በወረዳ የተጠናከረ የሰው ሀይል አደረጃጀት አለመኖር፤የወረዳ ኔት ውዝፍ ዕዳ ሳይከፈል መቆየቱ ፤ከሚኒስተር መ/ቤት ሲደገፍ የነበሩ የማህበረሰብ መረጃ ማዕከላትና የገጠር ኢኮቴ ማዕከላት ፕሮጀክቱ ዘለቀታ አገልግሎት መስጠት ያለመቻሉ የዘርፉ ዋና ዋና ክፍተቶች/ችግሮች ናቸው።እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት በቀጣዩ የእቅድ ዘመን ከፍተኛ የሆነ ትኩረት በመስጠት ቀጣይ ስራዎች እንዲከናወኑ አስፈላጊ ግብዓቶችን ማሟላት ዋናዉ ተግባር አድርጎ ይሰራል።